ቀን፡ / /200 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት

ደብረ ማርቆስ፣

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት

አዲስ አበባ፣

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባዔ

አዲስ አበባ፣

==========================================

**ጉዳዩ፡- በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥር ባለች ገዳም ስም ስለተጻፈ የክህደት መጽሐፍ አስፈላጊው ምላሽ እንዲሰጥበት ስለመጠየቅ፣**

==========================================

ከላይ በጉዳዩ ለመግለጽ እንደተሞከረው በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥር በምትተዳደር አንዲት ቤተክርስቲያናችን አሳታሚነት አንድ የክህደት መጽሐፍ ታትሞ በመሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ መጽሐፍ "ወልደ አብ" በመባል የተሰየመ ሲሆን አሳታሚዋም ጥንታዊቷ ገዳም "ምስካበ ቅዱሳን ቆጋ ኪዳነ ምሕረት አፀደ ኤዎስጣቴዎስ አንድነት ገዳም" እንደሆነችና ያሳተሙትም "መምህር ገብረ መድኅን እንዳለው" እንደሆኑ በመጽሐፉ ላይ ሰፍሯል፡፡ ይህ መጽሐፍ **በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን** አስተምህሮ ውስጥ የሌለ እንግዳ ትምህርት የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ በሐዋርያት ትምህርት ላይ የታነፀችው ቅድስት እና ንጽሕት ቤተክርስቲያናችን ከዚህ ቀደም በነበሩ ሊቃውንቷ ተነግሮ የማያውቅ እግዚአብሔር በአጸፋቸው መጽሐፎቿም ውስጥ ተጽፎ የማይገኝ እንግዳ ትምህርት በዚህ መልኩ ታትሞ መሠራጨቱ በክርስቲያኖች ዘንድ የእምነት ሕጸጽን የሚፈጥር መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ስለዚህም ብፁአን አባቶቻችንና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በጥልቀት እና በስፋት የምትመለከቱት እና ተገቢውን መልስና መፍትሔ የምትሰጡበት እንደሆነ እናምናለን፡፡ ሆኖም ግን ለመነሻነት ያህል በተወሰነ መልኩ መጽሐፉ ላይ የሰፈሩትን የተወሰኑ ክህደቶችን እንደሚከተለው እንዘረዝራለን፡፡

- ገጽ 127 ላይ "እንደ ዘርአ ብእሲ የሆነው ወልድ ነው ማለት እንዴት ነው ቢሉ፡፡ ከአባት ዘር ከእናት ደም ተከፍሎ ተዋሕዶ እንዲፈጠር ወልድም ከእግዝእትነ ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከተከፈለ ደመ ድንግልና ጋራ ተዋሕዶ <u>ተፈጥሯልና</u>" ብለው ወልድን ተፈጠረ በማለት ገልጸዋል፡፡
- ገጽ 130-131 "<u>ወልድ በሰውነቱ ፍጡር ይባላል</u>፡፡ ወልድንማ ፍጡር ብንለው እንደአርዮስ ክህደት አይሆንብንም ቢሉ አርዮስ በመለኮቱ ፍጡር ቢለው ክህደት

ሆነበት እንጅ በሰውነቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ባልሆነበትም ነበር። ነገር ግን በመለኮቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ሆነበት" በማለት ከተዋሕዶ በኋላ ፍልጠትን ደግፈው ጽፈዋል።

- ሁለቱን ልደታት እናምናለን የሚለውን የሊቃውንት ትምህርት ወደ ጎን በመተው በሁለት ልደታት የተሸፈነ ሦስት ልደታትን እንደሚያምኑ ይገልጻሉ። ይህም ገጽ 216-217 ላይ "የጌታችን ልደቱ ስንት ነው ቢሉ <u>ሁለት</u> ነው። እንዴት <u>ሁለት</u> ነው እምቅድመዓለም በመለኮቱ ተወለደ ብለናል ኋላም በማኅጸን በሰውነቱ ከአብ ተወለደ እንላለን ዳግም ከእመቤታችን በስጋ በጎል ተወለደ እንላለን ይህማ ሦስት አይደለምን እንደምን ሁለት ነው ቢሉ <u>እምቅድመዓለም በመለኮቱ የተወለደው ልደትና ዛሬ በማኅጸን በሥጋ በቅብአተ መንፈስ ቅዱስ የተወለደው ልደት አንድ ልደት ይባላል እንጅ ሁለት አይባልም</u>። ሁለት ጊዜ ቆጥረነው አንድ ማለታችን እንዴት ነው ቢሉ እምቅድመዓለም በመለኮቱ የወለደው አብ ነው። ዛሬም በሰውነቱ በማኅጸን የወለደው አብ ነው እንጅ ሌላ አይደለም። ወላዲው ተወላዲው ዛሬም የተወለደበት መንፈስቅዱስ ያ የጥንት የባሕርይ ሕይወቱ ስለአልተለወጠ አንድ ልደት ይባላል እንጅ ሁለት ልደት አይባልም።ለዚህም ምሳሌ ያስረዳል ምሳሌ እንዴት ያስረዳል ቢሉ እነሆ ዛሬ ሰው <u>አዲስ ሸማ ለብሶ ያነን በከረጢት ከቶ ዳግመኛ አውጥቶ ቢለብሰው አንዱን ሸማ ሁለት ጊዜ ለበሰው ተብሎ አንድ ሸማ ይባላል እንጅ ሁለት አይባልም</u>። ዳግመኛ <u>በአንድ ዘውድ ሁለት ሦስት ነገሥታት ቢነግሡበት ሁለት ሦስት ነገሥታት ነገሡበት ተብሎ አንድ ዘውድ ይባላል እንጅ ሁለት ዘውድ አይባልም</u>" በዚህ አስተምህሮ ውስጥ ልደትን ሁለት ነው ብለን እናምናለን ቢሉም በሊቃውንቱ መጻሕፍት ዘንድ ተጽፎ የማይገኝ አንድ ልደት ጨምረው ጽፈዋል። ይኸውም <u>"በማኅጸን በሰውነቱ ከአብ ተወለደ እንላለን"</u> በማለት የገለጹት ነው። ይህ ልደት በሊቃውንት መጻሕፍት ውስጥ የማይገኝ እንግዳ ትምህርት ነው።
- ገጽ 182 ላይ "መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ሆነ ማለት ምሥጢሩ ምንድን ነው ቢሉ ተሠጠ ማለት ነው። መሠጠቱ ወርቅ ተመዝኖ ከብት ተቆጥሮ እህል ተሰፍሮ እንዲሰጥ እንደዚያ ተሰጠ ማለት ማለት ነውን ቢሉ እንዲህስ አይደለም። እንዴት ነው ቢሉ <u>ጥንተ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ለወልድ በሰውነቱ የባሕርይ ሕይወት ሆነው ማለት ነው</u>። በእንተዝ ይትበሃል ከመ ነሥአ መንፈስ ዚአሁ ዘተነግረ በኢሳይያስ ነቢይ እንዘ ይብል መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌየ ቀብዓኒ በእንተዝ ሰበከ እንዘ ይብል እስመ መንፈስ ዘዚአየ በህላዌ ለሊሁ ኀደረ ላዕሌየ በእንተ ዝንቱ ወለምንትኑ ተሰመይኩ መሢሐ እንበለ ዳዕሙ ሶበ ኮንኩ ሰብአ እን ሳዊሮስ ዘአንጾ ሃ አ ክ ፱ ቁ፲፰" በማለት የራሳቸውን ትርጉም ሰጥተው ጽፈዋል።
- ገጽ 212 ላይ "በቅብአት የባሕርይ ልጅ ሆነ ማለት ምሥጢሩ ምንድን ነው ቢሉ ወልድ <u>በሰውነቱ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስን በመላ ተቀብሎ ከአብ የባሕርይ ልደት ተወለደ ማለት ነው</u>። ምነው ይህስ ቢሆን ወልድ በአብ ያልተወለደ በራሱ ያልተወለደ ስለምን በመንፈስ ቅዱስ ተወለደ ቢሉ ይህስ ወላዲ

በሚመስለው ሕይወት ይወልዳል እንጅ በማይመስለው አይወልድም፡፡ ለዚህም ምሳሌ ያስረዳል እነሆ ዛሬ በደመ ነፍስ ሕያዋን የሆኑ እንስሳ ከእንስሳ ይወለዳሉ በነባቢትም ነፍስ ሕያው የሆነ ሰው ከሰው ይወለዳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለአብ ሕይወቱ ነው በደመ ነፍስ ሕያው ያልሆነ ከእንስሳ በነባቢት ነፍስ ሕያው ያልሆነ ከሰው እንዳይወለድ፡፡ እንደዚህም ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ያልሆነ ከአብ አይወለድምና ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ከአብ ተወለደ" በማለት ጽፈዋል፡፡

- ወልደ አብ ገጽ 219 ላይ ደግሞ "ይህ የጸጋ ልጅነት የሌለው ባእድ ሥጋ እምቅድመ ዓለም የባሕርይ ልጅነት ካለው መለኮት ጋራ ቢዋሐድ የቃልን ገንዘብ ተቀብሎ ወልደአብ ቃለ አብ ቃለ መንፈስ ቅዱስ ሆነ ልጅነት አገኘ፡፡ ይህ ልጅነት ያለው ቃል ልጅነት ከሌለው ሥጋ ጋራ ቢዋሐድ በሥጋ ርስት ልጅነትን የሚሻ ሆነ፡፡ እንዘ ባዕል ውእቱ በኩሉ እንደየ ርእሶ እን ጳውሎስ ፪ኛ ቆሮ ም፰ ቁ፱ ስለዚህ ከእምቅድመ ዓለም ልደቱ ፩ድ ለማድረግ በሰውነቱ የባሕርይ ህይወቱን በመላ ተቀብሎ ከአብ ተወለደ እንጅ የቀደመ ልጅነቱስ አልተነሣውም፡፡ <u>ወልድስ በሰውነቱ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ተቀብሎ ባይወለድ ወልድ በሰውነቱ እንደ አብ ባልገዛም አብም ለወልድ በሰውነቱ አገዛዙን ክብሩን በመላ በሰፋ ባልሰጠውም ነበር</u> ኢይሁብ ክብርየ ለባዕድ ለተሳትፎ ወስብሐትየ ለግልፎ እን ኢሳ ም፵፪ ቁ፰ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ተቀብሎ ቢወለድ ግን እንደአብ ገዛ አዘዘ፡፡ አብም ለወልድ በሰውነቱ አገዛዙን ክብሩን ሰጠው አኮ ዘይሁብ እግዚአብሔር አብ መንፈሶ በመስፈርት አላ አብሰ ያፈቅር ወልዶ ወኩሎ ኩነኔሁ አወፈዮ ለወልዱ ውስተ እዴሁ እን ወን ዮ ም፫ ቁ፴፬፡፡ ወረሰዮ ወራሴ ለኩሉ እን ጳው ዕብ ም፩ ቁ፪" በማለት መጻሕፍትን በመቆንጻጸልና እንደራሳቸው ፈቃድ በመተርጎም ጽፈዋል፡፡
- ገጽ 232 ላይ ተዋሕዶን ሲነቅፉ "ተዋሕዶ ክብር የሚያሳልፍ ንዴትን የሚያጠፋ መስሏቸው የቃልን ክብር ለሥጋ ካሳለፍን ብለው <u>ለመንፈስ ቅዱስ ቦታ ቢያጡለት በተዋሕዶ ከበረ ቅብአት አልረባውም ብለው ተነሥተዋል</u>፡፡ ለሲህ ምን ይመልሷል ቢሉ <u>ተዋሕዶማ ሁለትነትን አጠፋ አንድነትን አጸና እንጅ ንዴትን አላጠፋም ክብርን አላሳለፈም</u>" ይላሉ ወልደ አብ
- ገጽ 230 ላይ ደግሞ ለመለኮት የማይቀጠል ቃል እንዲህ ብለው ቀፀሉ "በዚህም በባሕርይ ልጅነቱ እኛ ብቻ ተጠቅመንበት አልቀረንም <u>እርሱም ተጠቀመበት</u> እንጅ" ብለው ለመለኮት ሊቀጸል የማይገባውን ቃል "<u>ተጠቀመበት</u>" በማለት ጽፈዋል፡፡
- ገጽ 233 ላይ "ቅብአቱስ እንደረባው <u>ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ እንደአስተካከለው</u>..." ብለው ወልድ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ እንዲሆን ያደረገው ቅብአት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በልጅነት የጨቅላ አእምሯችን ከመጽሐፉ ውስጥ እንደመነሻነት ከላይ የዘረዘርናቸውን የክህደት ትምህርቶችን ገለጽን እንጅ መጽሐፉ በሙሉ በክህደት የተሞላ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ መጽሐፍ በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተሰራጭቶ በካህናትና በምእመናን እጅ

...ሯት በፊት አስፈላጊውን መፍትሔ እንድትሰጡን እንጠይቃለን፡፡ በአሁኑ ሰዓት ... መጽሐፍ በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሥር በሚተዳደሩ ገዳማት ውስጥ “ምስካበ ቅዱሳን ቆጋ ኪዳነ ምሕረት አፀደ ኤዎስጣቴዎስ አንድነት ገዳም" (ጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ) እና በ "መካነ ቅዱሳን አቡነ ዐሥራተ ማርያም አንድነት ገዳም" (ጎዛምን ወረዳ) ውስጥ በድብቅ እየተሸጠ የሚገኝ ሲሆን አዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን አካባቢ በግልጥ ከሌሎች መጻሕፍት ጋር አብሮ ተደርድሮ እየተሸጠ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ምእመናንም በየዋህነት እየገዙ እየተጠቀሙበት እንደሆነ ታውቋል፡፡

ስለዚህ ብጹአን አባቶቻችን እና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይህንን የክህደት ትምህርት ተመልክታችሁ አስፈላጊውን መፍትሔ በመስጠት የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ ትጠብቁ ዘንድ እና ምእመናንንም ባልተበረዘው ባልተከለሰው የቤተክርስቲያናችን እውነተኛ ትምህርት ታንጹ ዘንድ የልጅነት ተማጽኖን ከታላቅ ትህትና ጋር እያቀረብን እኛ በዚህ መልኩ ብጹአን አባቶቻችንንና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ሳይገባን ማሳሰባችንን እንደ ኃጢአት እንዳትቆጥሩብን ከታላቅ ይቅርታ ጋር እንለምናችኋለን፡፡

ነባብያን በጎች የተባሉ ምእመናንን ትጠብቁ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሥልጣን እና አደራ የተሰጣችሁ አባቶች ሆይ! በዚህ የተበረዘ አስተምህሮን በያዘ መጽሐፍ ምእመናን እንዳይሰናከሉ የጠባቂነት አደራችሁን ለልጆቻችሁ ታሳዩን ዘንድ እንማጸናችኋለን፡፡ ይህንን መጽሐፍም በማሰራጨት ላይ ያሉ ገዳማትን ከዚህ ግብራቸው እንዲቆጠቡ እንድታሳስቡልን በልጅነት ፍቅር እንለምናቸኋለን፡፡ መጽሐፉን በማሳተም የገንዘብ ወጭ የተደረገው ከ“ምስካበ ቅዱሳን ቆጋ ኪዳነ ምሕረት አፀደ ኤዎስጣቴዎስ አንድነት ገዳም" መሆኑ ተረጋግጦ ይህን የክህደት መጽሐፍ ለማሳተም ወጭ የተደረገው ገንዘብ ተመርምሮ ገንዘቡን ወጭ ያደረጉ አካላት በሕግ የሚጠየቁበት መንገድ ቢመቻች፡፡

**“እግዚአብሔር አምላክ ሀገራችንን ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን እንዲሁም እምነታችንን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን በሰላም በአንድነት በፍቅር ይጠብቅልን”**

**አሜን፡፡**

**“ወስብሐት ለእግዚአብሔር”**